የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

# ከሰሜን አሜሪካ የኢትዮጲያ እስረኛች አንድነት ኮሚቴ የወጣ ጋዜጣዊ መግለጫ

ሕዳር 30 ቀን 2003 (ዲሴምበር 6, 2010)

ከተለያዩ የዩናይትድ ስቴትስና ካናዳ ክልል የተገኙበት አባላት ሶስት ተከታታይ የቴሌ ኮንፍረንስ በማድረግ በዋነኛው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ስር የሚንቀሳቀስ የሰሜን አሜሪካ ቅርጫፍ ቻርተር ማዋቀራችንን ስንገልጽ በደስታ ነው። ቅርንጫፉ አስራ አንድ የቦርድ አባላትን ሲያቅፍ የስራ አስኪያጁ ኮሚቴ ደግሞ አምስት አመራር ሰጭ አባላትን ያካትታል።

- ላለፉት አስራ አምስት አመታት አለም አቀፉ ኢእአኮ ያለመታከት በግፈኞች ጭቆና ስር ለወደቁት ድምጽ በመሆን ሲሟገትላቸው አስተውለናል።
- በሱዳን በኬኒያ በጁቡቲና በየመን በኢሰብአዊ ሁኔታ በደል ለሚደርስባቸው ስደተኞች ድምጹን ከፍ በማድረግ አለም አቀፋዊ ትኩረት እንዲደረግላቸው ሲሟገት አይተናል።
- የዘመኑ ባርነት ሰለባ ለሆኑትና በአረብ አገር በግፍ የሚማቅቁ እህቶቻችን ሁኔታ ገሃድ በማድረግ ሲሟገትላቸውም አስተውለናል።
- ይህ የሰብአዊ መብት አስጠባቂ ኮሚቴ በሃይማኖት በፖለቲካ በባህል በዘር ላይ ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ሲሟገት አስተውለናል።

አለም አቀፉ የ ኢእአኮ የጀመረውን ከባድ ሃላፊነት በመጋራትና የሰብአዊ መብት የማስጠበቅ ትግሉን ለማገዝ የሰሜን አሜሪካ ቻርተር መመስረቱ ተገቢና የግድም አስፈላጊ መሆኑን አምነናል። ድርጅቱ አሁን ካለው ተሰሚነትና ጥንካሬ የበለጠ እንዲጎለብት በየአህጉሩ ተመሳሳይ ቻርተሮች/ቅርንጫፎች እንዲመሰረቱም ጥሪያችንን እናቀርባለን።
በሌላ በኩል ደግሞ ካልጠፋ ስም በኢእአኮ ስም ለመንቀሳቀስ የሚዋልለው በካናዳ አለሁ ባለ ባለአንድ አባል " ድር/ጅት" እንካን ለፓለቲካ እስረኞችና ስደተኞች ሊሟገት ቀርቶ የሌላ ድርጅት ስም በህገወጥ መንገድ መጠቀሙ በራሱ ስህተተና ውዥንብር መፍጠር መሆኑንም ያመነ አይመስልም። የሰብአዊ መብት እንዲከበር ከተፈለገ እንደዚህ አይነቱ ውዥንብርና ኣፍራሾች ገለል ማለት እንዳለባቸው የሰሜን አሜሪካ የኢእአኮ ከልብ ያምናል። በሰሜን አሜሪካ ብቸኛው የአለም አቀፍ የ ኢእአኮ ቻርተር መሆናችንን እናረጋግጣለን።
የኢእአኮ አላማ ግቡን ይመታ ዘንድ የስብዓዊ መብት ተቆርቋሪዎች ሁሉ ትብብርና ድጋፍ ወሳኝ ነው!

soceppna@gmail.com